# የግዳጅ ውትድርና ትዕዛዝ

ሶስተኛ አመት ሆነን የሴሚስተሩን ዕረፍት ያሳለፍኩት ወደ ቤተሰብ በመሄድ በድሬዳዋ ነበር፡ ሆኖም ግን አንድ ቀን አስቸኳይ መልዕክት ከዶርሜቶቼ ደረሰኝ (በስልክ ሊሆን ይችላል - ያውም በቀበሌው ስልክ በኩል)፡ **"አደገኛ የሆነ ለብሔራዊ ውትድርና ተማሪዎች ስም ዝርዝር የያዘ ማስታወቂያ ወጥቷል እና ወደዚህ እንዳትመለስ፡ እንዳውም እዛም ብትሰወር ጥሩ ነው፡ ስማቸው የወጣ ተማሪዎች ግቢውን ለቀው እየሄዱ ነው"** ምድር ሰማዩ ተገለባበጠብኝ፡ ወቅቱ የምስራቁ ጦርነት በድል ተደምድሞ የሰሜን ግን እያየለ የመጣበት ነበር፡ ወደ ሰሜን የሄዱ ሁሉ ሞት ነው የሚጠብቃቸው፡ 'ምርጫዬ ምንድነው?' እያልኩ ማሰላሰል ጀመርኩ፡ በቅርቡ አንድ ዘመዳችን ከብሔራዊ ውትድርና ማሰልጠኛ ጠፍቶ ወደ ጅቡቲ ለመሄድ ሲዘጋጅ እኛ ቤት ተደብቆ ለቀናት ከቆየ በኋላ በእግር የ6 ቀን ጉዞ ጅቡቲ መግባቱን አይቻለሁ፡ እኔስ በዛ መንገድ ለመሄድ ወኔው አለኝ? በፍፁም አላስበውም፡ ከዚህ ቤት ወጥቼ ሌላ ከተማ አንዱ ዘመድ ቤት ልደበቅ ብል የቤተሰብ እገዛ ይፈልጋል፡ በዚህ መሀል ጭንቀቴን ከፊቴ ላይ ያነበቡ ቤተሰቦች ምን እንደተፈጠረ ሲጠይቁኝ ነገርኳቸው፡ "በሀገር የመጣ ነገር ነው!" አይነት ሁኔታ ሳይ ተስፋዬ ተሟጠጠ፡ ሶስተኛው ምርጫ ወደ ውትድርና ብገባ፣ የተማርኩ በመሆኔ ወደ አንዱ ቴክኒክ ክፍል በመመደብ ከግንባር ጦርነት ላመልጥ እችል ይሆን ብሎ ማሰብ ነበር፡ ምን መተማመኛ አለው ግን? ከራሴ ጋር በከፈትኩት ጉባኤ ውስጥ አንዱን ሀሳብ ሳወጣ አንዱን ሳወርድ ውዬ አደርኩና አንድ ቀን እንደገና ዶርሜቶቼ ሲገሰግሱ መጡና **"ጥሪው ተሰርዟል"** የሚለውን ማስታወቂያ ሰጡኝ፡ እነሆ እስካሁን ይዣታለሁ፡ ኮፒው እንደ ኤግዚቢት ለዕይታ ቀርቧል፡


መጋቢት 17 ቀን 1976 ዓ.ም.

ለ፣ ተማሪዎች በሙሉ

የኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ. ተልዕኮ ይሣካል!!

አናሸንፋለን!!

ወደ ግቢ ተመልሼ ትምህርት እንደወትሮው ቀጠለ፡ ይህንን ክስተት በተመለከተ ከ41 አመት በኋላ የአለማያን 85 ተመራቂዎች ተሰባስበን ማስታወሻዎች ስንቀያየር፡ እነ ጀማል ሀሰንና አዱኛ ደረጀ የሚከተለውን መረጃ በዌብ ሳይታችን እንዳወጣው ነገሩኝ፡ እስከማስታውሰው ድረስ ከ3ኛ አመት መደበኛ ተማሪዎች ሎተሪ የወጣልኝ እኔ ብቻ ስሆን ሌላ ታከለ የሚባልም ልጅ ስም ዝርዝር ውስጥ የነበረ እና ያኔ እንደወጣ ሳይመለስ የቀረ መኖሩን ተሾመ ነግሮኛል።

## Adugna: Eyewitness-1

While we were in our third year, a shocking announcement was made by the government through the University’s administration. Some students were off campus because of the short break. On that fateful day, the entire student body gathered in front of the administrative building to fiercely oppose the military government’s attempt to forcibly conscript students from our college. Fear and uncertainty hung over us as we assembled, and when the military personnel sent to collect the selected student tried to address the crowd, his

speech was instantly drowned out by loud, defiant protests that shattered his bravado. I particularly remember Aklilu Woldu, our senior in Animal Science, standing up to the officers with remarkable boldness and volume. Later, when we joked that he could have been killed, he simply replied, “I was ready to take any bullets fired at me if that’s what it took to save my fellow students.”

At that critical moment, Azage Tegegn, then the Academic Dean of the college, stepped forward and rose to the occasion with extraordinary leadership. He reassured the students, saying, “This is an academic institution where students come to learn and develop the skills they need to contribute positively to their country. You are here on a mission to pursue your academic goals. No one will take that away from you. If necessary, I will resign. Now go, continue your studies, and we will resolve this issue with the officials.”

And so, we turned back, stood our ground, and ultimately thwarted the military government’s attempt to save our own Melaku💪. Azage played a central role in this outcome, and he should be remembered for his courage and leadership at a moment when even his own life was at risk.

**የዚህ ሰቆቃ ሳይረሳ ነው ታዲያ አራተኛ አመት መጨረሻችን አካባቢ ወደ ሰፈራ ጣቢያ እንድንዘምት የተደረገው፡ ከአካባቢው በሽታ ብንተርፍ ከግዳጅ ውትድርና ተርፈን እንመለሳለን ብሎ ያሰበ አልነበረም፡ የግቢውን ቀውስ በድፍረት በመጋፈጥ ዶ/ር አዛገ ተገኘ እንደታገለው ሁሉ በጋምቤላው ዘመቻ ላይም የዶ/ር በየነ ጭጭአይበሉ ትግል የሚረሳ አይደለም፡**